የሰ/መ/ቁጥር 153894

ሐምሌ 19 ቀን 2010 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ፈይሳ ወርቁ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስራት ፈንታ

ተጠሪ፡- አቶ ዩሐንስ ሃይሌ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቶአል።

# ፍርድ

ጉዳዩ የጋብቻ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ጋር ተያያዞ የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኗ አመልካች ላይ በጋምቤላ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው።

የክሱ ይዘትም በአመልካችና ተጠሪ ከ 1985 ዓ/ም ጀምሮ በባልና ሚስትነት አብረው የኖሩ ቢሆንም ልጅ ያልወለዱ በመሆኑ በመካከላቸው ያለመግባባት ባለመኖሩ ጤናማ ኑሮ መኖር ያልቻሉ መሆኑን ገልጸው ፍቺ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪም ቀርበው ተገቢ ነው ያሉትን መልስ የሰጡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙ ታርቀው ጋብቻቸውን እንዲቀጥሉ ይቻል ዘንድ ጉዳዩን ወደ ሽማግሌ መርቶ ይኼው ባለመሳካቱ በግራ ቀኙ መካከል የነበረውን ጋብቻ እንዲፈርስ ወስኖአል። ከዚህም በኋላ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ በማን በኩል እንደቀረበና ዝርዝሩ ቀርቦ ግራ ቀኙ ክርክር ማድረጋቸውን የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገብ ግልባጭ የማያሳይ ሆኖ በንብረቱ ላይ አፈጻጸም እንደቀጠለና አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠው ትእዛዝም ተገቢ ያለመሆኑን በመግለጽ የአሁኗ አመልካች ለጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይኼው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የንብረት ክፍፍል አፈጻጸም ውሳኔ ማጽናቱን የሚያሳይ ውሳኔ ቁጥሩ ባልተጠቀሰ መዝገብ በ 16/02/2010 ዓ/ም ሰጥቶአል። ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የበታች ፍርድ ቤቶች የጋብቻ ውጤት የሆነው የንብረት ዝርዝር ሳይቀርብና ግራ ቀኙ ተገቢውን ክርክርና ማስረጃ ሳያቀርቡ በጋምቤላ ከተማ 05 ቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኘውንና ጋብቻ ከፈረሰ በኋላ አመልካች በግል የሰሩትን ቤት የጋራ ነው በማለት መወሰኑ ያላግባብ መሆኑን፣ በጋምቤላ ከተማ ውሃ ልማት አከባቢ ያለውን ቤት በትዳር ጊዜ የተገዛ ሁኖ እያለ መታለፉ የአላግባብ ነው፣ በደንቢ ዶሎ ከተማ ውስጥ ያለው ቤት፣ የቡና አትክልትና ባህርዛፍ የተጠሪ የግሉ ነው

ተብሎ መወሰኑ ያላግባበ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ ካሁኗ አመልካች ጋር ያላቸው ጋብቻ እንዲፈርስ ክስ አቅርበው ጋብቻው በፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዲፈርስ የተደረገ ሲሆን ከዚህ በኋላ የጋብቻ ውጤት የሆነው የንብረት ዝርዝር ቀርቦ ግራ ቀኙ ማስረጃ አሰምተውና ፍርድ ቤቱም በተገቢው ማስረጃ ሁሉ አጣርቶ ዳኝነት የሠጠ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የማያሳይ መሆኑን ነው፡፡ የጋብቻ ውጤት የሆነው ንብረት ክፍፍል ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው ግራ ቀኙ በስምምነት ያደረጉት ክፍፍል ሲኖር ወይም ፍርድ ቤቱ በሕጉ አግባብ የቀረቡትን ማስረጃዎችን ሰምቶና ፍሬ ነገሩን በሚገባ አጣርቶ ስለመሆኑ የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 68/2000 በአንቀጽ 87፣ 95 እና 96 ስር ከደነገጋቸው ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

እንግዲህ ከአመልካችና ከተጠሪ የጋብቻ ውጤት ነው በማለት ከሚያቀርቡት የንብረት ክፍፍል ክርክር አንጻር ንብረቱ መኖር ያለመኖሩና የግል ወይም የጋብቻ ውጤት መሆን ያለመሆኑን የሚመለከቱ ጭብጦች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 246፣ 247 እና 248 ድንጋጌዎች አንጻር ተይዘው እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን በሚያቀርበው የክርክር ይዘት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 258 እና 259 በተደነገገው አግባብ የማስረዳት ግዴታ አለባቸው፡፡ ሆኖም አመልካችም ሆነ ተጠሪ  አከራካሪዎቹን ንብረቶች ላይ ተገቢ ነው ያሉትን ክርክርና ማስረጃ ስለማቅረባቸው ሳይረጋገጥ በደፈናው የተሠጠ ውሳኔ መሆኑን ከበታች ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ግልባጮች ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን ማስረጃ ከማስረጃው አግባብነት፣ተቀባይነት እና የማሳመን ብቃት አንጻር በማየት የማይቀበለው ሆኖ በመገኘቱ ምክንያት ሳይመለከተው የቀረ ካልሆነ በቀር ክርክርን በማስረዳት የቀረበን የተከራካሪ ወገን ማስረጃ በዘፈቀደ ውድቅ ማድረግ እንደማይቻል ስለማስረጃ አቀባበል በተደነገጉት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ  138፣257፣ 258 እና 259 ድንጋጌዎች ስር ተመልክቷል፡፡ ይህም የተከራካሪ ወገንን የመደመጥ መብት ለማስከበር ሲባል የተዘረጋ ሥርዓት መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

እንዲሁም የበታች ፍ/ቤት ወይም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በክርክርና ክርክርን ለማስረዳት የቀረበን፤የተሰማን ማስረጃ አንድ በአንድ በማገናዘብ በመተቸት፤ የሚቀበለውንና የማይቀበለውን በመለየት ዳኝነት መስጠት እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 181 እና 182 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው የሕጉ አገላለጽ የሚያስረዳ ሲሆን ይህ የማስረጃ አቀባበል አካሄድ ፍርድ ቤቱ በፍርድ አፃፃፍ ወቅት የግድ ሊከተለው የሚገባው መሆኑን የተጠቃሽ ድንጋጌዎች ይዘት ያሳያል፡፡የበላይ ፍ/ቤትም ይህ ዳኝነት የፍርድ አፃፃፍ ስህተት የማስረጃ አቀባበል ሥርዓት ጉድለት መፈፀሙን የሥር ፍ/ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ የሚያስረዳና ሳይመረመርና ሳይታይ የታለፈው የማስረጃ ይዘት በመዝገቡ ላይ ሰፍሮ ከተገኘ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 342 መሰረት በዚሁ የመዝገብ ግልባጭ ላይ በመመርኮዝ አስፈላጊውን ዳኝነት መስጠት እንደሚቻልም በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም የአሁኗ አመልካች ከላይ በሰበር አቤቱታቸው ላይ ስለተጠቀሱት ንብረቶች  የጋብቻ ውጤት ወይም የግል ንብረቶች ተለይቶ የሚወሰነው የግራ ቀኙ ማስረጃዎች በህጉ አግባብ ተሰምተውና ፍሬ ነገሩ በሚገባ ተጣርቶ ነው፡፡ በሕግ አግባብ በተቆጠረ ማስረጃ ፍሬ ነገሩ

ሳይጣራና ያለ ሕጋዊ ምክንያት ማስረጃው ሰይሰማ የንብረት ክፍፍል ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት፣ ማስረጃው ቀርቦ ደግሞ ይዘቱ ሳይታይ በደፈናው ውድቅ የሚደረግበት የማስረጃ አቀባበል ስርዓት ተቀባይነት የሌለው ሲሆን የክርክሩ ፍሬ ነገሮች አግባብነት ባላቸውና በሕጉ አግባብ በተቆጠሩ የተከራካሪ ወገኖች ማስረጃዎች እንዲሁም አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ደግሞ በፍርድ ቤቱ አነሳሽነትም ከሚመለከታቸው አካላት በሚቀርቡት ማስረጃዎች በተገቢው መንገድ ሳይጣሩ ዳኝነት መስጠት የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የማይቀበለው ጉዳይ ሲሆን የክርክሩ አካሄድ ሳይሟላ የሚሰጥ ዳኝነት ደግሞ በውጤቱ የተከራካሪ ወገኖችን የመደመጥ መብት እጅጉን የሚጎዳ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው።ሲጠቃለልም፡-

1. በጋምቤላ ከተማ 05 ቀበሌ ውስጥ ያለው ቤት ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ የተሰራ ነው ወይስ አይደለም?
2. በጋምቤላ ከተማ ውሃ ልማት አከባቢ ያለው ቤት በትዳር ውስጥ የተፈራ ነው ወይስ አይደለም?፣
3. በደንቢዶሎ ከተማ ያለው ቤት፣ የቡና አትክልትና ባህርዛፍስ የተጠሪ የግል ንብረት ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ አለ? ወይስ የለም? ሌሎች

ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነትና አስፈላጊነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች በአመልካች በተቆጠሩት ማስረጃዎች፣ፍርድ ቤቱ አስፈለጊ ሲሆን ሌሎች ማስረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ራሱ በማስቀረብ ጭምር ጉዳዩን በተገቢው መንገድ አጣርቶና የፍሬ ነገሩን ክርክር አሟልቶ፣ በሕጉ የተመለከተውን የፍርድ አፃጻፍ ስርዓት በመከተል ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መመለሱ ስነ ስርዓታዊ ሆኖ አግኝተናል። በዚህም ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የጋራ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን በተመለከተ የሠጡት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

## <u>ውሣኔ</u>

1. በጋምቤላ ከተማ አስዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በጋምቤላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የጸናውና ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል።
2. የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ የንብረት ዝርዝር በማቅረብ ክርክሩን እንዲቀጥል አድርጎ በፍርድ ሐተታው ላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ማስረጃዎችን በመስማትና በተገቢው መንገድ ሁሉ ፍርድ ቤቱ በሚያስቀርባቸው ማስረጃዎች ጭምር በማጣራት ጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት መልሰንለታል።ይፃፍ።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክረ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።**